# በወንጌል ተልዕኮ አገልግሎት ላለመሳተፍ ለሚቀርቡ ምክንያቶች የተሰጡ ምላሾች

ስለ ሚስዮን (የወንጌል ተልዕኮ) ሥናገር÷ የተወሰኑ ሰዎችን ወደፊት በወንጌል ተልዕኮ(ሚስዮናዊነት) እንዳይራመዱ ለሚያግዷቸው እክሎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ ለመስጠት ሞክሬለሁ። እግዚአብሔር እነዚህን ምላሾች በመጠቀም ብዙዎቻችሁን እንዲጠራችሁና እንድትሄዱ ጸሎቴ ነው። ከዚህ በመቀጠል ስምንት ምክንያቶችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሾችን እናገኛለን።

1. "ብቁ አይደለሁም።"

"ጠቢብ የት አለ? ሊቅስ የት አለ? የዘመኑስ ፈላስፋ የት አለ? እግዚአብሔር የዓለምን ጥበብ ሞኝነት አላደረገምን? ከእግዚአብሔር ጥበብ የተነሳ ዓለም በገዛ ጥበብዋ እግዚአብሔርን ማወቅ ስለ ተሳናት፣በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ያድን ዘንድ የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኗል።" (1 ቆሮንቶስ 1፡20-27)

"ወንድሞች ሆይ፤ በተጠራችሁ ጊዜ ምን እንደነበራችሁ አስቡ። በሰው መስፈርት ብዙዎቻችሁ ዐዋቂዎች አልነበራችሁም፤ ብዙዎቻችሁም ኀያላን አልነበራችሁም፤ ብዙዎቻችሁም ከትልቅ ቤተሰብ አልተወለዳችሁም። ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን ያሳፍር ዘንድ የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፤ እግዚአብሔር ብርቱዎችን ያሳፍር ዘንድ የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ።" (1 ቆሮንቶስ 1፡26-27)

2. "አካሌና ስዕብናዬ ጠንካራ አይደለም።"

"ነገር ግን ይህ እጅግ ታላቅ ኃይል ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ አለመሆኑን ለማሳየት፣ ይህ የከበረ ነገር በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን።" (2 ቆሮንቶስ 4፡7)

"እርሱ ግን (ክርስቶስ)፣ "ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኀይሌ ፍጹም የሚሆነው በድካም ጊዜ ነውና" አለኝ። ስለዚህ የክርስቶስ ኀይል በእኔ ያድር ዘንድ፣ ይበልጥ ደስ እያለኝ በድካሜ እመካለሁ። ስለ ክርስቶስ በድካም፣ በስድብ፣ በመከራ፣ በስደትና በጭንቀት ደስ የምሰኘው ለዚህ ነው፤ ስደክም ያን ጊዜ ብርቱ ነኝና።"

(2ቆሮንቶስ 12፡9-10)

3. "አንደበተ ርቱዕ አይደለሁም።"

"ክርስቶስ የላከኝ ወንጌልን እንድሰብክ እንጂ እንዳጠምቅ አይደለም፤ የክርስቶስ መስቀል ከንቱ እንዳይሆን፣ በሰዎች የንግግር ጥበብ አልሰብክም።" (1 ቆሮንቶስ 1፡17)

"ሙሴም እግዚአብሔርን ጌታ ሆይ፣ ቀድሞም ሆነ፣ አንተ ከባሪያህ ጋር ከተነጋገርህ ወዲህ፣ ከቶ አንደበተ ርቱዕ ሰው አይደለሁም። እኔ ኮልታፋና ንግግር የማልችል ሰው ነኝ" አለው። እግዚአብሔርም ሙሴን፣ "ለሰው አንደበቱን የሰጠ ማነው? ሰውን ደንቆሮ ወይም ዲዳ የሚያደርገው ማነው? ዐይን የሚሰጥ ወይም ዕውር የሚያደርገውስ ማነው? እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን? በል አሁን ሂድ፤ እኔ እንድትናገር አደርግሃለሁ፤ የምትናገረውንም አስተምርሃለሁ" አለው። (ዘጸአት 4፡10-12)

4. **“በጋዜጣዎች ላይ የማነባቸው ዘግናኝ ታሪኮች ያስፈሩኛል።”**

“ራሳችሁን የምትገዙ ሁኑ፤ ንቁም፤ ጠላታችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚያገሳ አንበሳ ወዲያ ወዲህ ይዞራል። በዓለም ዙሪያ ያሉት ወንድሞቻችሁ ተመሳሳይ መከራ እንደሚቀበሉ ዐውቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት። በክርስቶስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ፣ ለጥቂት ጊዜ መከራ ከተቀበላችሁ በኋላ እርሱ ራሱ መልሶ ያበ ረታችኋል፤ አጽንቶም ያቆማችኋል።” (1ጴጥሮስ 5:8-10)

5. **“ፍሬያማ አልሆንም ብዬ እፈራለሁ።”**

ከአንተ የሚጠበቀው ታማኝነት እንጂ ፍሬያማነት አይደለም።

“ከዚያም፣ (ኢየሱስ) እንዲህ አለ፤ “የእግዚአብሔር መንግስት ይህን ትመስላለች፤ አንድ ሰው መሬት ላይ ዘር ይዘራል። ሰውዬው ሌሊት ይተኛል፤ ቀን ይነሳል ነገር ግን እርሱ ሳያውቅ ያ ዘር በቅሎ ያድጋል፤ ምድርም ራስዋ በመጀመሪያ ቡቃያዋን፣ ቀጥሎም ዛላውን፣ ከዚያም በዛላው ላይ የጎመራ ፍሬ ታስገኛለች፤ ፍሬው እንደ በሰለም መከር በመድረሱ፣ ሰውዬው ወዲያው ማጭዱን አንስቶ አጨዳ ይጀምራል።” (ማርቆስ 4:26-29)

“እኔ ተከልሁ፤ አጵሎስ አጠጣ፤ ያሳደገው ግን እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ፣ የሚተክልም ሆነ ውሃ የሚያጠጣ አይለም።” (1 ቆሮንቶስ 3:6-7)

6. **“እዚህ ብዙ የሚሰራ ነገር አለ።”**

እውነት ነው ነገር ግን የስራ ክፍፍል አለ። እግዚአብሔር ለወንጌል ስርጭት ብቻ ሳይሆን አንዳንዶችን ለሚስዮናዊነት ይጠራል። ልዩነቱ በሮሜ 15:19-24 ላይ ይታያል።

“ከኢየሩሳሌም እስከ እልዋሪቆን ዙሪያ ድረስ የክርስቶስን ወንጌል ፈጽሜ ሰብኬአለሁ...ክርስቶስ ባልተጠራበት ስፍራ ወንጌልን መስበክ የዘወትር ምኞቴ ነበር...አሁን ግን በእነዚህ አካባቢዎች የምሰራው ስለሌለ፣ ከብዙ አመታት ጀምሮ እናንተን ለማየት እናፍቅም ስለ ነበር፣ ይህን ዕቅድ ወደ ስፔን በምሄድበት ጊዜ ልፈፅመው አስባለሁ።”

በዚህ አካባቢ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ወንጌልን ሊሰሙ ሲገባቸው፣ እንዴት ጳውሎስ በእነዚህ አካባቢዎች የምሰራው ስለሌለ ሊል ቻለ? ምክንያቱም ወንጌል ስርጭት **ሚስዮንነት** ስላልሆነ።

7. **“አላገባሁም”**

ምርጥ የትዳር አጋር የሚገኘው በመታዘዝ ነው።

“ጠባየ መልካምን ሚስት (ባል) ማን ያገኛታል (ያገኘዋል)? ከቀይ ዕንቁ እጅግ ትበልጣለች (ይበልጣል)።” (ምሳሌ 31:10)

ማግኘት እጅግ አስቸጋሪ ነው። በመታዘዝ መንገድ ላይ ግን ይሆናል።

8. **“ለወንጌል ተልዕኮ በሄድኩበት ሥፍራ ሁኔታዎች ተቀይረው ስህተት እሰራና በኃፍረት ወደ ቤቴ እመለሳለሁ ብዬ እፈራለሁ።”**

   የትኛው ይከፋል? በትጋት ክርስቶስን በወንጌል ተልዕኮ ለመከተል ማፈር÷ ወይስ አደገኛ ሁኔታዎችን ለመጋፈጥ መፍራት? በሰዎች ፊት ስህተትን ስለ መስራት ማፈር አይጎዳችሁም፤ ትሁትና በአዲስ ሁኔታዎች ውስጥ ጠቃሚ ያደርጋችኋል እንጂ። ነገር ግን ፍርሃት በሁሉም ቦታ የማትጠቅሙ ሰዎች ያደርጋችኋል።

   መክብብ 11፡4 በማንበብ የሚመጡ ነገሮችን ስለመፍራት የሚለውን ተመልከቱ።

   “ነፋስን የሚጠባበቅ አይዘራም፤ ደመናትንም የሚያይ አያጭድም።”

   **ትርጉም፡** ዘሩን ንፋስ ይወስደዋል ብለህ ለመዝራት ካልደፈርክ÷ ዝናብ ሰብሉን ያጠፋብኛል ብለህ አጨዳን ካልፈፀምክ÷ በረሃብ ትሞታለህ።

   ኦ! ነፃ አውጪው የእግዚአብሔር ቃል እንዴት ድንቅ ነው።

   **በመጋቢ ጆን ፓይፐር!**